የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRTIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ/ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th year No. 21
ADDIS ABABA 4th February 2009

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፷_፪ሺ፩
የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ … ገጽ ፬ሺ፬፻፶

## CONTENTS

Regulation No 160/2009
National Lottery Administration Re-Establishment Council of Ministers Regulation ………… page 4450

## ደንብ ቁጥር ፩፻፷/፪ሺ፩
## *የብሔራዊ ሎተሪ አስተደደርን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ*

በተካሄደው የመሠረታዊ የአሠራር ሥርዓተ ለውጥ ጥናት ግኝት መሠረት የብሔራዊ ሎተሪ አስተደደር እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ የሚያስፈልገው ሆኖ በመገኘቱ፣
የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲየዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ያወጣውን አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አወጅ ቁጥር ፮፻፫/፪ሺ፩ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ ፰ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩ *አጭር ርዕስ*

ይህ ደንብ የብሔሪዊ ሎተሪ አስተዳደርን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 1111 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪ *ትርጓሜ*

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካለሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

፩ "ሎተሪ" ማለት የሽልማት አሸናፊው በዕድል በዕጣ አወጣጥ ወይም በማንኛውም ሌላ ዘዴ የሚታወቅበት ጨዋታ ወይም ድርጊት ሲሆን ቶምቦላን ወይም ራፍልን፣ ሎቶን፣ ቶቶን፣ ፈጣን ሎተሪን፣ የቁጥር ሎተሪን፣ የተደራራቢ ሽልማት ሎተሪን የኘሮሞሽኘ ሎተሪን፣ ቢንጎን፣ የስፖርት ውርርድ ሎተሪንና ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶችን ይጨምራል፣

## REGULATION NO.160/2009
## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLISHMENT OF NATIONAL LOTTERY ADMINISTRATION*

WHEREAS, it is become necessary to re-establish the National Lottery Administration in accordance with the findings of the business process re-engineering study:
NOW THEREFORE, this regulation is issued by the council of Ministers in accordance with Article 2(8) of the definition of powers and Duties of the Executive organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Amendment Proclamation No 603/2008.

## PART ONE
## GENERAL

### *1. Short Title*

This Regulation may be cited as the National Lottery Administration Re-establishment Councils of Ministers Regulation No 160/2009"

### *2. Definitions*

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1 "Lottery" means any game or activity in which the prize winner is determined by chance, drawing of lots or by any other means and includes tom bola or raffle, lotto, Toto, instant lottery, number lottery, multiple prize lottery, promotional lottery, bingo, sport betting lottery and other similar activities.

፪ "የገንዘብ ሎተሪ" ማለት ሽልማቱ በገንዘብ የሚሰጥ ሎተሪ ነው፣

፫ "ቶምቦላ ወይም ራፍል" ማለት የሎተሪ ቲኬቶቹ ቅድሚያ ተከታታይ ቁጥር ተሰጥቷቸው የሚታተሙ፣ አሸናፊው በሕዝብ ፊት በሚወጣ ዕጣ የሚለይና ሽልማቱ ፊት በሚወጣ ዕጣ የሚለይና ሽልማቱ በዓይነት የሚሰጥ ሎተሪ ነው፣

፬ "የስፖርት ውርርድ ሎተሪ "ማለት በቤት ውስጥ ወይም ከቤት ውጭ የሚከናወኑ የስፖርት ውድድሮችን መሠረት በማድረግ የሚደረግ ውርርድና ሽልማቱ በገንዘብ ወይም በዓይነት የማሰጥ ሎተሪ ነው፣

፭ "ሎቶ" ማለት አስቀድሞ ከተለዩ ተከታታይነት ካላቸው ቁጥሮች መካከል ተጫዋቹ የሚፈልጋቸውን የተወሰኑ ቁጥሮች በመምረጥ አሸናፊ መሆን አለመሆኑ በሕዝብ ፊት በሚወጣ ዕጣ የማወሰንበት የገንዘብ ሎተሪ ነው፣

፮ "ቶቶ" ማለት በዋናነት በእግር ኳስ ጨዋታ ወቅት በሚደረግ ውርርድ ሽልማቱ በገንዘብ የሚሰጥ፣ እና

ሀ/ ከተወራረዱት መካከከል ብዙ አሸናፊዎች የሚኖሩ ከሆነ ለሽልማቱ የተመደበው ገንዘብ ለአሸናፊዎቹ አኪለ የሚከፈል፣ ወይም

ለ/ ውድድሩ በተባለው ሰዓት ሳይካሄድ ውጤቱ ቢሰረዝ ወይም የጨዋታው ዓይነት ቢለወጥ አሸናፊዎገቹ በሕዝብ ፊት በሚወጣ ዕጣ የማለዩበት፣ሎተሪ ነው፣

፯ "ፈጣን ሎተሪ" ማለት ተሳታፊዎች የሎተሪውን ቲኬት በመፋቅ ሽልማቱን ማግኘት ወይም ማጣታቸውን ወዲያውኑ የሚያቁበት የገንዘብ ሎተሪ ነው፣

፰ "የቁጥር ሎተሪ" ማለት የሎተሪው ቲኬቶቹ በቅድሚያ ተከታታይ ቁጥር ሰጥቷቸው የሚታተሙና አሸናፊው በሕዝብ ፊት በሚወጣ ዕጣ የሚለይ የገንዘብ ሎተሪ ነው፣

፱ "የተደራራቢ ሽልማት" ሎተሪ ማለት ተሳታፊው አንድ የሎተሪ ቲኬት ከዋናው ሽልማት ሌላ ተጨማሪ ሽልማት የሚያገኝበት የገንዘብ ሎተሪ ነው፣

2 "Money lottery" means a lottery in which the prize is distributed in money

3 "tombola or raffle" means a lottery in which lottery tickets are given serial numbers, winners are determined by public draw and prizes are distributed in kind

4 "sport betting lottery" means a lottery for betting arranged on the basis of indoor or out door sport competitions and in which the prize is distributed in money or in kind

5 "lotto" means a money lottery in which chance of winning is determined by choosing certain numbers from a defend series of numbers and in which the winning numbers are determined by public draw

6 "Toto" means a money lottery performed by betting at a time where there is mainly

a) where there are several winners of a single event, the prize money is divided equally among the winners: or

b) where the event does not take place at eh specified time, the results are cancelled or its competitive nature is changed, winners are identified by public draw,

7 'Instant lottery' means a money lottery in which participants can determine immediately whether they won or lost prizes by scratching the lottery tickets

8 'Number lottery' means a money lottery in which lottery tickets are given serial numbers and winners are determined by public draw

9 'Multiple prize lottery' means a money lottery in which a participant may win an additional prize besides the main prize by the same lottery ticket

፲ "ኮንቬንሽናል ቢንጎ" ማለት በቢንጎ ማጫወቻ ክበብ በመገኘትና በቅድሚያ ካርድ በመግዛት ተሳታፊዎች ከአጫዋቹ የሚሰጡ ትዕዛዞችን ከራሳቸው የመጫወቻ ቁጥሮች ጋር እያመሳከሩ አሸናፊ መሆን አለመሆናቸው የሚታወቅበት የገንዘብ ሎተሪ ነው፣

.፲፩ "ዘመናዊ ቢንጎ" ማለት ተሳታፊዎች በሎተሪ ቲኬቶች ላይ የሚሰጡ ትዕዛዞችን መሠረት በማድረግ የዕድል ቁጥሮች ከመጫወቻ ቁጥሮች ጋር እያመሳከሩ አሸናፊ መሆን አለመሆናቸው የሚታወቅበት የገንዘብ ሎተሪ ነው፣

.፲፪ የኘሮሞሽን ሎተሪ ማለት የምርት ወይም የአገልግሎት ሽያጭን ለማስፋት በምርት መጠቅለያ ወይም ክዳን ውስጥ ተደብቀው የሚገኙ ዕጣዎችን፣ከምርቱ ወይም ከአገልግሎቱ ግዢ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚታደሉና ባለዕድል የማያደርጉ ኩፖኖችንᎄ ካርዶችን ወይም ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም የሚከናወን ሽልማት በዐይነት የሚሰጥ ሎተሪ ነው፣

.፲፫ "የሎተሪ ሥራ" ማለት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ማናቸውንም ዓይነት ሎተሪ በማዘጋጀት በሀገር ውስጥ መሸጥ፣ማከፋፈል፣ ማጫወትና ዕጣ ማውጣት ወይም ማናቸውንም ተመሳሳይ ተግባር ማከናወን ነው፡፡

.፲፬ "ሰው" ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

.፲፭ "ባለሥልጣን እና የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ ኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ነው፣፣

## ክፍል ሁለት

## የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር

### ፫ *እንደገና መቋቋም*

፩ የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር /ከዚህ በኃላ አስተዳደር እተባለ የሚጠራ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

፪ የአስተዳደሩ ተጠሪነት ለባሥልጣኑ ይሆናል፡፡

### ፬ *ዋና መስሪ ቤት*

የአስተዳደሩ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን እንደ አስፈላጊነቱ በአገሪቱ ውስጥ በማናቸውም ቦታ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

10 'Conventional bingo' means a money lottery in which participants go to bingo game centers and buy cards in which they correspond their numbers with the numbers communicated by the game setter and determine whether the won or lost prizes

11 'Modern bingo' means a money lottery in which participants can determine whether they won or lost prizes by corresponding the luck numbers with play numbers following instruction given on lottery tickets.

12 'Promotional lottery' means a lottery designed to promote the sale of products or services by the use of lots hidden in product packaged or covers, luck coupons and cards distributed along with the sale of the goods or services or any other methods and the prize of which is distributed in kind

13 'Lottery activity' means the preparation of any lottery inside or outside the country and the distribution sale, drawing of lots of the performance of any other similar activity inside the country.

14 'person' means and natural or juridical person

15 'Authority' and Authority's Director General" means the Ethiopian Revenues and Customs Authority and Director General of the Authority respectively.

## PART TWO

## THE NATIONAL LOTTERY ADMINISTRATION

### 3 *Re-establishment*

1 The National Lottery Administration (hereinafter referred to as the administration) is herby re-establish as an autonomous federal agency having its own legal personality.

2 The Administration shall be accountable to the Authority.

### 4 *Head office*

The Administration shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere in the country as may be necessary.

## ፭ ዓላማ

የአስተዳደሩ ዓላም ሎተሪን በማካሄድ ለኢኮኖሚና ማኀበራዊ ልማት እገዛ የሚያደርግ ገቢ ማመንጨትና የሎተሪ ሥራን መቆጣጠር ይሆናል፡፡

## ፮ የአስተዳደሩ ሥልጣንና ተግባር

አስተዳደሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ የሎተሪ ሥራን ያካሄዳል፣ ዕጣ የሚወጣበትን ቀን፣ የሽልማቱን መጠንና ሁኔታ፣ ሽልማቱ የሚቆይበትን የጊዜ ገደብና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በሎተሪ ትኬቶተ ላይ ያመለክታል፡ አሸናፊ የዕጣ ቁጥሮችንም ለሕዝብ ያስታውቃል፣

፪ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከልዩ ልዩ የሎተሪ ዓይነቶች ከሚገኘው ገቢ ላይ ለዕድለኞች መክፈል ያለበት ድርሻ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፣

፫ የአሸናፊ ዕጣ የተከፈለባቸውን ከሽያጭ የተረፉ የሎተሪ ቲኬቶች በውጭ ኦዲተር ከተመረመሩ በኃላ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ ያደርጋል፣

፬ በዚህ ደንብ በደተነገገው መሠረት ለሎተሪ ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፣

፭ የሎሪን ጨዋታ ለማካሄድ የማያስፈልጉ የመሣሪየ ዓይነቶችንና መመዘኛዎችን ይወስናል፣ ወደ አገር ውስጥ የማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣

፮ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

፯ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ሕጋዊ ተግባራትን ያከናውናል፣

፰ ህገወጥ የሎተሪ ሥራዎችን ይቆጣጠራል፡፡

## ፯ አስተዳደሩ አቋም

**አስተዳደሩ**

፩ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፣

፪ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የማሾም ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና

፫ አስፈላጊው ሥራተኞች ይኖሩታል፣

## 5 Objectives

The objectives of the Administration shall be to generate, through undertaken lottery activities, revenue that could contribute in financing the country's economic and social development programs and to supervises lottery activities

## 6 Powers and Duties of the Administration

The Administration shall have the powers and duties to!

1 undertake lottery activities indicate on lottery tickets the drawing dates of lots amounts and conditions of prizes, period of limitations for claiming prizes and other necessary information, and announce winning numbers to the public

2 The objectives of the Administration shall be to generate, through undertaken lottery activities, revenue that could contribute in financing the country's economic and social development programs and to supervises lottery activities

3 dispose winning and settled as well as unsold lottery tickets after being audited by external auditors in accordance with the directive to be issued by the Authority

4 give permit to undertake lottery activities, supervise the same and revoke in accordance with the provisions of this Regulation

5 determine the types and specifications of equipment required to perform lottery games, issue permits fro and supervise the importation of the same

6 own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name,

7 perform other legal activities necessary for the attainment of its objectives.

8 control illegal lottery activities.

## 7 Organization of the Administration

**The Administration shall have:**

1 a Director General to be appointed by the Government upon the recommendation of the Director General of the Authority,

2 a Deputy Deputy Director General to be appointed by the Director General of the Authority and

3 the necessary staff.

## ፰ የዋና ዳይሬክተር እና የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩ ዋና ዳይሬክተሩ ከባለሥልጣኑ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የአስተዳደሩን ስራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

፪ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ዳይሬክተር፣

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የአስተዳደሩን ስልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፣

ለ/ የአስተዳደሩን ድርጅታዎ መዋቅር፣ የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ይውላል፣

ሐ/ ለአስተዳደሩ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፣

መ/ የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፭/፲፱፻፺ ፱ ቢኖርም ከአስተዳደሩ የሥራ ባህሪ አንፃር በባለሥልጣኑ በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት የአስተዳደሩን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሠ/ የአስተዳደሩን ሠራተኞች ልዩ የደመወዝ ስኬልና የጥቅማጥቅም ክፍያ አጥንቶ በባለሥልጣን በኩል ለመንግሥት ቀርቦ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፣

ሰ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከፍርድ ቤት ውጭ ክርክሮችን በስምምነት ይጨርሳል፣

ረ/ ከሦስት ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ አስተዳደሩን ይወክላል፣

ሸ/ አዳዲስ የሎተሪ ጨዋታዎችን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ጥናቶችን ለባለሥልጣኑ እያቀረበ ያስወስናል፣

ቀ/ የአስተዳደሩን የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፡፡

፫ ዋናው ዳይሬክተር ለአስተዳደሩ ሥራ ቅልጥፈና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለአስተዳደሩ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጠ ይችላል፡፡

፬ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ከዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጥ መመሪያ መሠረት ፡-

## 8 *Powers and Du6ies of the Director General and Deputy Director General*

1 The Director General shall, subject to the general directives of the Authority ,direct and administer the activities of the Administration

2 Without prejudice to the prevision of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a/ exercise the powers and duties of the Administration stated under Article 6 of this Regulation

b/ prepare and submit to the Authority the organizational structure, work plans and budgets of the administration and, upon approval, implement the same,

c/ effect payments in accordance with the approved budget of the Administration.

d/ notwithstanding the Federal Civil Servant Proclamation No 515/2007, based on the nature of the business of the administration employ and administer employees in accordance with the directive to be issued by the Authority

e/study and submit to the government through the Authority, a special salary scale and employment benefit schemes of the employees of the Administration and , upon approval, implement the same,

f/ represent the Administration in all its dealings with third parties

g/settle disputes out of court as may be necessary

h/ submit studies on the introduction of new lottery games fro the approval of the Authority.

i/ prepare and submit to the Authority the activities and finical reports of the Administration

3 The Director General may, to the extent necessary for the efficient performance ot the activities of the Administration, delegate part pf his powers and duets to other officials and employees of the Administration

4 The Deputy Director General shall, subject to the directives of the Director General

ሀ/ የአስተዳደሩን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተርን ያግዛል፣

ለ/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ለዋና ዳይሬክተሩ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣

ሐ/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል።

### ፱ ***የገቢ ምንጭ***

አስተዳደሩ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፣

፩ የሎተሪ ቲኬት ሽያጭ፣

፪ ከጋራ ሽርክና ሥራ የሚገኝ ገቢ እና፣

፫ የፈቃድና የኮሚሽን ክፍያዎች።

### ፲ ***የገቢ አጠቃቀም***

፩ ከአስተዳደሩ ገቢ ላይ ለሎተሪ ዕድለኞች የተከፈለውና ለሥራ ማስኬጃ የዋለው ከተቀነሰ በኃላ የሚቀረው የተጣራ ገቢ አስተደደሩ የሚዘው የመጣባበቂያ ሂሳብ ብር ፩ ሚሊዮን /አንድ ሚሊዮን ብር/ እስከሚሆን ድረስ ወደዚሁ ሂሣብ ገቢ ይደረጋል።

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው የመጠባበቂያ ሂሣብ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ለሎተሪ ዕድለኞች ክፍያ ለመፈጸም የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥም ብቻ ይሆናል።

፫ የመጠባበቂያ ሂሣብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪ ለተመለከተው ዓላማ በመዋሉ ምክንያት የጐደለ እንደሆነ ከአስተደደሩ የተጣራ ገቢ ላይ እየተቀነሰ እንዲተካ ይደረጋል።

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ወይም /፫ የተመለከተው ተቀናሽ ከተደረገ በኃላ ተራፊው ሂሣብ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ያደርጋል።

፭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፬/ መሠረት/ ፈሰስ የተደረገው ሂሣብ በአስተዳደሩ ስም በመንግስት ለሚታቀዱ የኢኮኖሚና ማህበራው ልማት ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ይውላል፡

### ፲፩ . ***ስለ ሂሣብ መዛግብት***

፩ አስተዳደሩ የጥንድ ሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመከተል የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል።

፪ የአስተዳደሩ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይመ እርሱ በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች ይመረመራሉ።

a/ assist the Director General in planning, organizing directing and coordinating the activities of the Administration.

b/ act on behalf of the Director General in his absence,

C/ Perform other activities assigned to him by the director General.

### 9 ***Source of Revenue***

The following shall be the Administration's sources of revenue

1 lottery ticket sales,

2 proceeds of joint venture activities and

3 permit and commission fees

### 10 ***Utilization of Revenue***

1 The Administration's surplus income after deduction is made fro prize payments and operating costs shall be retained as reserve fund until the amount of such fund reaches birr 1,000,000 (One Million Birr)

2 The reserve fund referred to in Sub-article (1) of this article shall be utilized only for settlement of lottery prize winners' claims in the event of cash shortages.

3 Where the reserve fund is utilized for the purpose referred to in sub-article (2) of this article. The administration's surplus income shall be retained until the fund is fully replenished

4 The residual surplus, after making the deductions referred to in sub-article (1) or (3) of this Article, shall be transferred to the central Treasury.

5 The residual surplus transferred to the Central Treasury pursuant to sub-article(4) of this Article shall be utilized for the execution of economic and societal development projects planned by the government in the name of the Administration.

### 11 ***Books of Accounts***

1 The Administration shall keep complete and accurate books of accounts by using the double entry accounting system.

2 The books of accounts and other financial documents of the Administration shall be audited by the Auditor General or by external auditors assigned by him.

# <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የሎተሪ ሥራ ስለማካሄድና ስለፈቃድ አሰጣጥ</u>

### .፲፪ *<u>የሎተሪ ስራ ስለማካሄድ</u>*

፩ አስተዳደሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ /፪/ ንዑስ አንቀጽ /፭/፣/፮/፣ /፯/፣ /፰/፣/፱/ ፣ እና /፲፩/ የተመለከቱትን የሎተሪ ዓይነቶች የሚካሄድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል፡፡

፪ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ቢኖርም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በባለሥልጣኑ ሲፈቀድ አስተዳደሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ /፪/ ንዑስ አንቀጽ /፭ እና /፮/ የተመለከቱትን የሎተሪ ሥራዎች የካፒታል፣ ቴክኖሎጂ ፣ የዕውቀትና የሥራ አመራር ብቃቱ ካላቸው ተሳታፊዎች ጋር በጋራ ሽርክና ሊያካሂድ ይችላል፡፡

፫ በዚህ ደንብ አንቀጽ /፪/ ንዑስ አንቀጽ /፫/ /፬/ ፣ /፲/ እና /፲፪/ የተመለቱት የሎተሪ ሥራዎች በማንኛውም ሰው በፈቃድ ሊካሂዱ ይችላሉ፡፡

### .፲፫ *<u>ለሎተሪ ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት</u>*

፩ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ /፲፪/ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሰረት የሎተሪ ሥራ ለማካሄድ ፈቃድ እንዲሰጠው ሲፈልግ ለዚህ ተግባር የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላትና አስፈላጊ ማስረጃዎችን በማያያዝ ማመልከቻውን ለአስተዳደሩ ያቀርባል፡፡

፪ አስተዳደሩ የቀረበለት የፈቃድ ማመልከቻ የተሟላ መሆኑንና ባለሥልጣኑ በመመሪያ ያወጣቸው ሁኔታዎችና ግዴታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የተጠየቀውን ፈቃድ ይሰጣል፡፡

### .፲፬ *<u>ፈቃድን ስለማገድና መሠረዝ</u>*

፩ ማንኛውም ባለፈቃድ የዚህን ደንብ ወይም ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን ድንጋጌዎች የጣሰ ወይም የፈቀደለት ውጭ የሠራ እንደሆነ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እስኪወሰድ ድረስ አስተዳደሩ ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል፡፡

፪ አስተዳደሩ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ማንኛውንም ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል፣

ሀ. ፈቃዱ የተገኘው ሁለተኛ ማስረጃ ወይም መግለጫ በመቅረቡ የሆነ እንደሆነ

# <u>PART THREE</u>

## <u>UNDERTAKING OF LOTTERY ACTIVITIES AND ISSUANCE OF PERMIT</u>

### *12 <u>Undertaking of lottery Activities</u>*

1 The Administration shall have exclusive right to undertaken lottery activities referred to in sub-article (5), (6), (7), (8), (9) and (11) of Article 2 of this Regulation.

2 Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the Administration may, where it is deemed necessary and upon obtaining the authorization of the Authority, undertake lottery activities referred to in sub-articles (5) and (6) of Article 2 of this Regulation with joint venture partners having the requisite capital, technology, know-how and managerial competence.

3 The lottery activities referred to in sub-article (3), (4), (10) and (12) of Article 2 of this Regulation may be undertaken by any person up on permit.

### *13 <u>Issuance of Permit</u>*

1 Any person seeking a permit for undertaking any lottery activity, pursuant to sub-article (3) of Article 12 of this Regulation, shall fill in the prescribed application form and submit to the Administration to gather with the necessary evidence.

2 The Administration shall, upon ascertaining the completeness of the application and the fulfillment of the terms and conditions set by the directives of the Authority, issue the requested permit.

### *14 <u>Suspension and Revocation of Permit</u>*

1 where any permit holder violated the provisions of this Regulation or directives issued for its implementation or acted outside the scope of the permit, the Administration may suspend the permit until the necessary corrective measure is taken.

2 The Administration may revoke a permit on any of the following grounds:

a. where the permit was obtained by producing false documents or declarations

ለ. ፈቃዱ የአስተዳደሩ ስምምነት ሳይኖር ለሌላ ሰው ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ

b. Where the permit is found to have been transferred to another person without the consent of the Administration

ሐ. ፈቃዱ የሕዝቡን ሰላምና ፀጥታ ወይም የአገሪቱን ደህንነት የሚጎዳ የወንጀል ተግባር ሲሰራበት ወይም የማጭበርበር ተግባር ተግባር ሲፈፅምበት ከተገኘ

c. Where the permit is used in pursuance of a criminal act against public peace and order or notional security or for committing any fraudulent act

መ. ፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ከታገደና ባለፈቃዱ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ባይወስድ ከቀረ

d. Where the permit has been suspended in accordance with sub-article (1) of this Article and the permit holder has failed to take the necessary corrective measure within the specified time limit,

ሠ. ባለፈቃዱ የንግድ ሥራውን የተወ ወይም የከሰረ እንደሆነ፣

e. Where the permit holder cases operating his business or becomes bankrupt.

ረ. በተሰጠው የጉዜ ገደብ ፈቃዱን ያላሳደሰ እንደሆነ፡፡

f. Where the permit holder fails to renew the permit within the permit within the specified time limit.

፫ የአስተዳደሩ አንደን ፈቀድ ከማገዱ ወይም ከመሠረዙ በፊት እርምጃውን የሚወስድበትን ምክንየት ለባለፈቃዱ በጽሑፍ በመግለጽ ባለፈቃዱ ጽሁፉ በደረሰው በሰባት ቀናት ውስጥ የበኩሉን አስተያየት በጽሑፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

3 Before suspending or revoking a permit, the Administration shall notify in writing the permit holder the reasons for taking such measure and invite him to submit a written response within seven days from the date of receipt of the notice.

፬ ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ በተለነጸው መሠረት መልስ ካልሰጠ ወይም የሰጠው መልስ

4 If the permit holder fails to reply as mentioned in sub-article (3) of this Article or if his response is not satisfactory, the Administration shall suspend or revoke the permit. Any person who is dissatisfied with the decision may lodge his appeal to the Authority.

## ፲፭ ስለፈቃድ እድሳት

## 15 *Renewal of Permit*

፩ ከአንድ ዓመት በላይ ለሚካሄድ የሎተሪ ሥራ የሚሰጥ ፈቃድ በየበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ መታደስ አለበት፡፡

1 Any permit issued for a lottery activity lasting for more than a year shall be renewed at the beginning of every fiscal year.

፪ ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ፈቃዱ የሚያገለግልበት የበጀት ዓመት ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ አለበት፡፡

2 An application fro renewal of permit shall be submitted one month before the end of the budget year for which it was issued.

፫ አስተዳደሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ መሰረት ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሠረዝ የሚያበቃ ምክንያት ካልኖረ በስተቀር ማመልከቻው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ያድሳል፡፡

3 The Administration shall renew the permit within 30 days of the submission of the application unless there is a ground for suspending or revoking it in accordance with Article 14 of this Regulation.

## ፲፮ *<u>ቁጥጥር ስለማድረግ</u>*

፩ አስተዳደሩ፣

ሀ. የዚህን ደንብና ደንቡን ለማስፈጸም የሚወጡ መመሪያዎች እንዲሁም ፈቃድ የተሰጠባቸው ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣

ለ. የኢንተርኔት ቴክኖሎጂን ወይም ማናቸውንም ሌላ ዘዴ በመጠቀም የዕድል ይዘት ያላቸው ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ ይቆጣጠራል፡፡

ሐ. ያለፈቃድ የሚካሄድ የሎተሪ ሥራን የማስቆም ትዕዛዝ ይሰጣል፣ ጥፋተኛውም በሕግ መሠረት እንዲቀጣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፡፡

፪ አስተዳደሩ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማውጣት በማናቸውም አመቺ ሰዓት ወደ ማንኛውም የሕንፃ ይዞታ በመግባት ህገ ወጥ የሎተሪ ሥራዎችን ይቆጣጠራል፡፡

## ፲፯ *<u>ክልከላ</u>*

፩ ማንኛውም ሰው ከአስተዳደሩ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው ማናቸውንም የሎተሪ ሥራ ማካሄድ አይችልም፡፡

፪ ማንኛውም ሰው የሎተሪ ሥራ ለማካሄድ የተሰጠውን ፈቀድ ያለአስተዳደሩ ስምምነት ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይችልም፡፡

## ፲፰ *ስለፈቃድ ክፍያዎች*

ስለፈቃድ ማውጫና ማሳደሻ የሚጠየቀው ክፍያ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፲፱ *የኮሚሽን ክፍያ*

፩ አስተዳደሩ የሎሪ ሥራ ለማካሄድ ፈቃድ ሲሰጥ ወይም ሊያድስ ከፈቃድ ክፍያው በተጨማሪ፡-

ሀ. ለቶምቦላ ወይም ለስፖርተ ውርርድ ሎተሪ ሲሆን ሎተሪው ቲኬት ሽያጭ ሊገኝ ይችላል ተብሎ በሚገመተው ጠቅላላ ገቢ፣

ለ. ለኘሮሞሽን ሎተሪ ሲሆን ለሽልማት ሊውል በታቀደው ምርት ወይም አገልግሎት ጠቅላላ የመሸጫ ዋጋ የገቢ ግብርን ጨምሮ፣ ወይም

ሐ. ለኮንቬንሽናል ቢንጎ ሲሆን ባለፈቃዱ በየጊዜው በሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ፣ ላይ ተሰልቶ ፲፭% የኮሚሽን ክፍያ ይሰበስባል፡፡

## 16 *<u>Supervision</u>*

1 The administration shall

a. make the necessary follow up and supervision to ensure the observance of this Regulation and directives that may be issued for the implementation of this regulation and the conditions of a permit

b. Control activities having chance elements not to be undertaken through the use of internet technology or any other means.

c. Issue an order to stop the carrying out of any unauthorized lottery activity and report to the concerned organs with a view to prosecuting the offender in accordance with the law.

2 The Administration may, up on having search warrant issued by court, enter into any premises at any convenient time to control illegal lottery activities.

## 17 *<u>Prohibitions</u>*

1 No person may undertake lottery activities without having a permit issued by the Administration.

2 It is prohibited to transfer a permit issued to undertake lottery activities without the consent of the Administration.

## 18 *Permit Fees*

Fees to be paid for the issuance and renewal of permits shall be prescribed by directives to be issued by the Authority.

## 19 *Commission Payments*

1 Where the Administration issues or renews permits to undertake lottery activates, it shall collect 15% commission payments in addition to permit fees calculated on:

a. In the case of tom bola or sport betting lottery, the forecasted total revenue from lottery tickets sales

b. in the case of promotional lottery, the total value of the products or services allocated for prize awards including income tax or

C. in the case of conventional bingo and any other lottery, the total periodical revenue earned by the permit holder.

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሐ/ የተመለከተው ሥራ የኮሚሽን ክፍያ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በተመከተው የጊዜ ገደብ ውሰጥ ሳይከፈል ከቀረ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ መሠረት ሊወስድ የሚችለው አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ክፍያው ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር የ፳% መቀጫ ያስከትላት፣ ሆኖም ጠቅላላ መቀጫው ከሚፈለገው የኮሚሽን ክፍያ ፻% ሊበልጥ አይችልም፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳ *ቅጣት*

ድርጊቱ በወንጀል ሕግ መሠረት የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተደክ፣

፩ ማንኛውም ሰው የጸና ፈቃድ ሳይኖረው የሎተሪ ሥራ ካካሄደ ከብር ፶ሺ. እስከ ፻ ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮና ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርሰ እሥራት ይቀጣል፣

፪ ማንኛውም ሰው፣

ሀ. የህንፃ ይዞታውን ለሕገ-ወጥ ሎተሪ ሥራ ማካሄጃ እንዲውል ያከራየ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የፈቀደ ፣ ወይም

ለ. በአስተዳደሩ ቁጥጥር እንዲያደርግ የመደበን ሠራተኛ ቁጥጥር ወደሚደረግበት የሕንፃ ይዞታ እንዳይገባ የከለከለ ወይም የቁጥጥር ሥራው እንዳይካሄድ በማናቸውም መንገድ ያሰናከለ፣

እንደሆነ ከብር ፲ሺ. እስከ ፳ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና ለአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት በሚደርሰ እሥራት ይቀጣል፡፡

### ፳፩. *መመሪያ የማውጣት ሥልጣን*

ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም የማያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

### ፳፪. *የመብትና ግዴታ ሥልጣን*

፩ የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር /፭፻፴፭/፲፱፻፺፱/ ይተዳደር የነበረው የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር መብትና ግዴታዎት በዚህ ደንብ ለአስተዳደሩ ተላልፈዋል፡፡

፪ ይህን ደንብ የሚቃረኑ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሠራር ልምዶች በዚህ ደንብ የሸፈኑ ጉዳዩችን በማመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

2 Without prejudice to any administrative measure that may be taken in accordance with Article14 of this Regulation, failure to settle a commission payment pursuant to sub-article (C) of this article within the time limit set by directives issued by the Authority shall result in a fine of 20% for every month for delay provided, however, that such fine shall not exceed 100% of the outstanding commission payment.

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### *20* *Penalty*

Unless the act entails higher penalty under the Criminal Law

1 any person who undertakes any lottery activity without having a valid permit shall be punished with a fine not less than birr 50,000.00 and not more than birr 100,000 and with an imprisonment for not less than three years and not more than five years

2 any person who

a. leases or authorizes in any other manner his premises for the purpose of carrying out any illegal lottery activity or

b. prohibits the Administration's inspector from entering into his premises for the purpose of conducting inspection or obstructs the inspection in any other manner,

shall be punished with a fine not less than birr 10,000 and not more than birr 20,000 and with an imprisonment for not less than one year and not more than two years.

### *21* *Power to Issue Directives*

The Authority may issue directives necessary for the proper implementation of this Regulation.

### *22* *Transfer of Rights and Obligations*

1 The rights and obligations of the National Lottery Administration being administered by the National Lottery Administration Re-establish proclamation No 535/1999 are hereby transferred to the Administration by this Regulation.

2 All laws, regulations, directives and practices inconsistent with the provisions of this Regulation shall have no effect on matters covered by this Regulation.

### ፳፫. ***ደንቡ የማጸናበት ጊዜ***

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ጠቅላይ ሚኒስትር**

### ***23 Effective Date***

This Regulation shall come into force upon the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.
Done at Addis Ababa this 4th day for February 2009.

**Done at Addis Ababa 4th day of February 2009.**

**MELES ZENAWI**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**